# ደንብ

## የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ግብአቶች፦ CGA-RA፣ IFA፣ IFA-RA፣ IKA፣ IKB-RA፣ IKC-RA፣ ISB-RA፣ JEA-RA፣ KBA-RA፣ KLA፣ KLA-RA

ኃላፊነት ያለበት ጽ/ቤት፦ Chief of Teaching, Learning, and Schools

## የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

I. ዓላማ

የተማሪዎችን ውጤት በትክክል መመዝገብ እና ሪፖርት የማድረግ ልምዶችን ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሜሪላንድ ስቴት ስርአተ ትምህርት እና ግምገማ ልምዶች ጋር ለማጣጣም

II. ትርጓሜ

A. የትምህርት ውጤት ምዘናዎች፦ ዲስትሪክት አቀፍ ፈተናዎችን፣ የክፍል መጨረሻ ፈተናዎችን፣ የመጨረሻ ሴሚስተር ግምገማዎችን፣ ፕሮጀክቶችን፣ አፈጻጸምን መሰረት ያደረጉ ግምገማዎችን እና ሌሎች ተመሳሳይ የተማሪን የክፍል ደረጃ ወይም የኮርስ ማቴሪያል የፈጠራ እና የድምር ውጤት ማሳያዎችን ያጠቃልላሉ፥ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም።

B. የማስረጃው አካል፦ ተማሪው/ዋ ተለይተው የተቀመጡትን የትምህርት ደረጃዎች ወይም ግቦች የሚመጥኑ ሥራዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ የትምህርት ሥራዎች ስብስብ ነው።

C. የሚጠበቁ የኮርስ ክንውኖች፦ በኮርሱ መጨረሻ ላይ ተማሪው/ዋ መቀዳጀት ያለበ(ባ)ት የችሎታ እና የእውቀት መገለጫዎች ናቸው።

D. የኮርስ ቡድን፦ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተመሣሣይ ኮርስ የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉ ናቸው።

E. በክፍል ደረጃ የሚጠበቁ፦ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት አይነት በክፍል ትምህርት መጨረሻ ላይ ሊያገኙት የሚገባቸው የክህሎት እና የእውቀት መገለጫዎች ናቸው—የአንደኛ ደረጃ ተማሪ የክፍል ትምህርቱ በሚጠናቀቅበት ጊዜ በአንድ የተወሰነ የትምህርት ዓይነት እና በክፍል/ርዕሰ-ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ላይ እንደተገለጸው ማወቅ የሚጠበቅበት እና ማከናወን የሚችለው መስፈርት ነው።

F. ማርክ መስጫ ክፍለጊዜ፦ በግምት የዘጠኝ ሳምንት ጊዜ ወይም ሩብ የትምህርት ዓመት ነው፣ ይኼውም ግለሰብ ተማሪው(ዋ) የተማራቸው ፅንሰ-ሀሳቦች እና ችሎታዎች ስኬት ሪፖርት የተደረገበት ወቅት ማለት ነው።

G. ሴሚስተር፦ በተለምዶ ለሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት ያላቸው ኮርሶች ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ነው፣ እና በግምት18-ሳምንት የሚፈጀው ጊዜ የሚያመለክተው ሁለት የ 9-ሳምንት የማርክ መስጫ ክፍለጊዜዎችን ወይም የአንድን የትምህርት አመት ሩብ ጊዜ ነው። በመጨረሻ ግለሰብ ተማሪ በዚያ ወቅት የተማረ(ች)ውን ፅንሰ-ሀሳቦች እና ችሎታዎች ስኬት ሪፖርት ይደረጋል።

H. ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፡- የመማር ጥንካሬያቸውና ፍላጎታቸው ላይ ተመስርቶ የማስተማር ዘዴ ለውጥ (እንደሁኔታቸው እየታየ የማስተማር ማስተካከያ የሚደረግላቸው፣ ልዩ መገልገያዎች የሚያስፈልጋቸው (accommodations) ተማሪዎች ቡድኖች ናቸው።

III. **ቅደም-ተከተሎች**

A. የተማሪ ትምህርት ማረጋገጫ

ከ MCPS ደንብ IFA-RA ጋር የሚጣጣም ሥርዓተ ትምህርት፥መምህራን ከጊዜ ወደ ጊዜ ልዩ ልዩ ዓይነት የምዘና ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች የ MCPS ሥርዓተ ትምህርት መማራቸውን ክትትል የሚያደርጉበት ማረጋገጫ ይፈጥራሉ። የተማሪዎች ውጤት በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው።

1. የመረጃዎቹ አካል የሚያካትተው መመዘኛ ውጤቶችን ማለትም የዩኒቱ ግምገማ፣ ጽሑፍ የሚቀርብባቸውን ትምህርቶች፣ ፕሮጀክቶችን፣አጫጭር ፈተናዎች ወይም ቴስቶችን፣ እና/ወይም የሥራ አፈጻጸማቸውን ውጤቶች ነው።

2. የማስረጃዎቹ አካል በ "MCPS Regulation IKB-RA" ላይ ከተገለፀው በስተቀር፣ ለልምምድ ወይም ለትምህርቱ ዝግጅት የተመደበን/የተሰጠን ስራ ላይጨምር ይችላል፣የቤት ሥራ ከንውኖች።

B. ውጤት (ማርክ)

1. ውጤቶች የሚገለጹት እያንዳንዱ በሚያሳየው ችሎታ እና የመረዳት አቅም ተመሥርቶ መሆን አለበት።

2. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ይዘት የክፍል ውጤቶች የሚመደቡት በክፍል ደረጃ ወይም በወሰዱት ኮርስ የሚጠበቅ እውቀት ማግኘታቸውን በተጨባጭ ሲረጋገጥ ነው።

3. በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውጤቶች የሚሰጡት የሚጠበቅባቸውን የኮርስ መስፈርቶችን መረጃ መሠረት ያደረገ ነው።

4. የክፍል ደረጃ ውጤት አሰጣጥ እና ከሚወስዱት ኮርስ የሚጠበቅ ውጤትን በተመለከተ በስርአተ ትምህርት ሰነዶች ላይ የተዘረዘሩ ሲሆን ሰክሽን III.D ላይ ተብራርቷል።

5. ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ESOL) የእንግሊዝኛ መምህራን፣ የልዩ ትም/አስተማሪዎች፣ እና ተማሪዎችን የሚያስተምሩ የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የተማሪን ውጤት ለመወሰን የሚሰበሰቡ ማስረጃዎችን በህብረት ይገመግማሉ።

6. በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አንድ ተማሪ አምስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ከቀረ(ች) እና በክትትል ጣልቃ-ገብነት እቅድ (AIP) መሰረት ማሻሻል ካላሳየ/ች በውጤት አሰጣጥ ስሌት ውስጥ ይመዘገባል፥ ካልሆነ ግን መቅረት እና አርፍዶ መምጣት/መዘግየት በዉጤት አሰጣጥ ስሌት ዉስጥ አይገባም። ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የ AIP ቅደም ተከተሎች በ MCPS ደንብ JEA-RA ውስጥ ተዘርዝረዋል፣ ስለ ተማሪ የትምህርት ክትትል።

7. በሪፖርት ካርዶች ላይ የሚመዘገቡ መደበኛ የውጤት አመዘጋገብ ምልክቶች እና መመዘኛዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

a) የመዋለ ሕፃናት እና የ 1ኛ ክፍል አካዳሚክ ዉጤቶች

| | |
|---|---|
| P | በዚህ ማርክ መስጫ ወቅት በተሰጠዉ የክፍል ደረጃ መስፈርቶች ብቃት አለው/አላት |
| I | በዚህ ማርክ መስጫ ወቅት የተሰጠዉን የክፍል ደረጃ መስፈርቶችን ለማሟላት በማሻሻል ላይ |
| N | በዚህ ማርክ መስጫ ወቅት የተሰጠዉን የክፍል ደረጃ መስፈርቶችን ለማሟላት ገና ግስጋሴ/መሻሻል አላሳየም/አላሳየችም ወይም መጠነኛ መሻሻል በማሳየት ላይ |
| M | መረጃዎች/አሃዞች አልተሟሉም - የተመዘገበ ውጤት የለም |
| NEP/የእንግሊዝኛ ብቃት ማነስ | የእንግሊዝኛ ብቃት የሌላቸው፡-በመጀመሪያዎቹ ሁለት የማርክ መስጫ ወቅቶች ወደ ዩ.ኤስ ት/ቤት የገቡ ደረጃ 1 እና ደረጃ 2 ESOL ተማሪዎች ለ NEP ብቁ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል። NEP የሚያመለክተው በዚህ የማርክ መስጫ ወቅት ተማሪው/ዋ በመመዘኛ ርዕስ በቂ ውጤት እንዳላሳየ/ች ነው። የ ESOL ደረጃ ምንም ይሁን ምን፣ ተማሪው/ዋ፣ በተወሰኑ የትምህርት ይዘት መስኮች የብቃት ችሎታ ማሳየት ከቻለ/ች፣ ዉጤቶች (ማለትም፣ P፣ I፣ N) ከ NEP ጋር ሪፖርት መደረግ አለበት። |

b) ከ 2ኛ ክፍል እስከ 5ኛ ክፍል አካደሚያዊ ውጤቶች

| | |
|---|---|
| A | ተማሪው/ዋ በዘላቂነት በዚህ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ መደበኛውን የክፍል ደረጃ ብቃት አሳይቷል/አሳይታለች። |
| B | ተማሪው(ዋ) ዘወትር በዚህ የማርክ መስጫ ወቅት የክፍል ደረጃ የሚመጥን ትምህርት በቂ ችሎታ አሳይቷል/አሳይታለች። |
| C | ተማሪው(ዋ) በዚህ የማርክ መስጫ ወቅት አልፎ አልፎ የክፍል ደረጃ ትምህርት የሚመጥን በቂ ችሎታ አሳይቷል/አሳይታለች። |
| D | ተማሪው(ዋ) በዚህ የማርክ መስጫ ወቅት የተማረውን/የተማረችውን የክፍል ደረጃ ትምህርት ብቃት ያሳየ(ች)ው እምብዛም ነው። |
| M | የተሟላ መረጃ የለም - የተመዘገበ ውጤት የለም |
| NEP/የእንግሊዝኛ ብቃት ማነስ | የእንግሊዝኛ ብቃት የሌላቸው፡- በመጀመሪያዎቹ ሁለት የማርክ መስጫ ወቅቶች ወደ ዩ.ኤስ ት/ቤት የገቡ ደረጃ 1 እና ደረጃ 2 ESOL ተማሪዎች ለ NEP ብቁ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል። NEP የሚያመለክተው በዚህ የማርክ መስጫ ወቅት ተማሪው/ዋ በመመዘኛ ርዕስ በቂ ውጤት እንዳላሳየ/ች ነው። የ ESOL ደረጃ ምንም ይሁን ምን፣ ተማሪው/ዋ ፣ በተወሰነ የትምህርት ይዘት የብቃት |

| | |
|---|---|
| | ችሎታ ማሳየት ከቻለ/ች ፣ ዉጤቶች (ማለትም፣ P፣ I፣ N) ከ NEP ጋር ሪፖርት መደረግ አለበት። |

c) ከ 6ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል አካደሚያዊ ውጤቶች

| | |
|---|---|
| A | 90-100 የላቀ የአፈፃፀም ደረጃ |
| B | 80-89 ከፍተኛ የአፈፃፀም ደረጃ |
| C | 70-79 ተቀባይነት ያለዉ አፈፃፀም ደረጃ |
| D | 60-69 ዝቅተኛ የአፈፃፀም ደረጃ |
| E | ተቀባይነት የሌለዉ የአፈፃፀም ደረጃ |
| E3 | በክፍል ውስጥ **አምስት** ወይም ከዚያ በላይ ያልተፈቀደ መቅረት ያላቸው ተማሪዎች |

d) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት ያላቸው ኮርሶች የሰሚስተር ውጤት ስሌት የሚደረገው በማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ 1 እና በ 2ኛው የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ላይ በመመስረት ነው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| AA = A* | BA = A | CA = B | DA = B | EA = C |
| AB = A | BB = B | CB = B | DB = C | EB = C |
| AC = B | BC = B | CC = C | DC = C | EC = D |
| AD = B | BD = C | CD = C | DD = D | ED = D |
| AE = C | BE = C | CE = D | DE = E** | EE = E** |

*ሡንጠረዥ እንዴት እንደሚነበብ ለምሳሌ፦ የሰሚስተሩ የመጀመሪያዉ ማርክ መስጫ ወቅት የተገኘ ውጤት A እና በሰሚስተሩ የሁለተኛዉ ማርክ መስጫ ወቅት የተገኘ ውጤት A በሰሚስተሩ መጨረሻ ዉጤት A ያስገኛል።

**እነዚህ ሁለት የዉጤት ሁኔታዎች በሰክሽን III.J.2 እንደተመለከተው ለክሬዲት ማሻሻያ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ

C. ስለ ተማሪ ክንውን ሪፖርት ማድረግ

1. የሪፖርት ካርዶች

a) የሪፖርት ካርድ እስከ ውጤት መስጫ ወቅት የተሰበሰቡትን የተማሪውን ክንውን መረጃዎች አሳጥሮ የያዘ ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፦

(1) ውጤቶች ከሚፈለገው የውጤት ሚዛን ጋር ወጥነት ያለው፣ የተማሪው(ዋ)ን በክፍል-ደረጃ/በኮርስ የሚጠበቁ ውጤቶች ላይ ስኬትን ያመለክታሉ።

(2) የትምህርት ክትትል፣ ከ MCPS ደንብ JEA-RA ጋር የሚጣጣም፣ የተማሪ የትምህርት ክትትል

(3) ከመዋለ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የተማሪዎች የመማር ችሎታ/ክህሎት

b) በግላዊ ሁኔታ የተቀረጹ የትምህርት ፕሮግራሞችን (IEP) ለሚከታተሉ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ከፌደራል እና ከስቴት ተፈላጊ/መስፈርቶች ጋር በሚፈለገው መሠረት፣ የሪፖርት ካርድ በሚሰጥበት ወቅት ወደ (IEP) ግብ ለመድረስ ያለውን እርምጃ የሚገልጽ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣቸዋል።

c) በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሪፖርት ካርዶች በክፍል ደረጃ የሚጠበቁ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ።

(1) ሪፖርት ካርድ የሚያንፀባርቀው የተማሪው(ዋ) ን ትክክለኛውን የትምህርት ደረጃ እና በምንባብ እና በሂሳብ የተሰጡትን ሥራዎች ክንውን ውጤት ነው።

(2) የ ESOL ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፥ ተማሪዎቻቸው በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመጻፍ ያላቸውን አፈጻጸም በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ፣ ይህም ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸው ጋር በሚስማማ መልኩ ነው።

2. መደበኛ የሪፖርት አሰጣጥ እንደሚከተለው በክፍል ደረጃ ይለያያል፦

a) የቅድመ ሙዋዕለ ህፃናት መምህራን የተማሪዎችን ክንውን በወላጅ ኮንፈረንሶች እና ገለፃ በሚያደርጉላቸው ወቅት ሪፖርቶችን ለወላጆች/ሞግዚቶች ያቀርባሉ።

b) K–5 ላሉት ክፍሎች የሪፖርት አሰጣጥ እንደሚከተለው ነው፦

(1) K–5 ክፍሎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሪፖርት ካርዶች የሚሰጡት በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት መጨረሻ ላይ ነው።

(2) K–5 ባሉት ክፍሎች፣ በአንደኛው ሴሚስተር ላይ አንድ የ "ወላጅ/መምህር ስብሰባ" ማድረግ ያስፈልጋል። የሚፈለግባቸውን ደረጃ የማያሟሉ ወይም ከሚጠበቅባቸው ደረጃ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ወላጆች ጋር ተጨማሪ ኮንፈረንስ መደረግ ይኖርበታል።

c) ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሪፖርት የሚሰጠው እንደሚከተለው ነው፦

(1) ከ 6ኛ እስከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የሪፖርት ካርድ የሚሰጠው በእያንዳንዱ የውጤት መስጫ ወቅት ማብቂያ ላይ ነው።

(2) የመካከለኛ ጊዜ ሪፖርቶች/Interim reports ለሁሉም ተማሪዎች ይላካሉ፥ ነገር ግን በመውደቅ ጠርዝ ላይ ያሉ ወይም ከባለፈው ውጤት ከአንድ አልፋቤት ማርክ በላይ ዝቅተኛ ለሚያመጡ ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸው ወላጆች/ሞግዚቶች የግድ መላክ ይኖርበታል።

(3) የመካከለኛ ጊዜ ሪፖርቶች/Interim reports የሚላኩት በአራተኛ እና በስድስተኛ የውጤት መስጫ ሣምንታት መካከል ነው። ተማሪው/ዋ በውጤት መስጫ ወቅት ወደ መጨረሻው ላይ በሚያሳየው/በምታሳየው ክንውን በጣም ከቀነሰ/ች መምህሩ(ሯ) ለወላጆች/ለሞግዚት ይህንኑ ማሳወቅ ይኖርበ(ባ)ታል።

(4) ከባለፈው የማርክ መስጫ ወቅት ተማሪው/ዋ ከአንድ አልፋቤት ፊደል የበለጠ ከቀነሰ/ች ወይም በመውደቅ ጠርዝ ላይ ካለ/ች የወላጅ/መምህር ኮንፈረንሶች ያስፈልጋሉ።

3. መምህራን በ MCPS ድረ ገጽ ላይ በስልክ ጥሪዎች፣ ኢሜይሎች ወይም በይለፍ ቃል በሚከፈቱ የመገናኛ ዘዴ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር እንዲገናኙ ይበረታታሉ።

4. የተማሪን ትምህርት የማሻሻል ሁኔታ በሚመለከት አሳሳቢ ሁኔታ ካለ እና ስለተማሪው/ዋ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ መምህራን ወይም ወላጆች/ሞግዚቶች ተጨማሪ ኮንፈረንሶች እንዲደረጉ መጠየቅ ይችላሉ።

5. መምህራን በቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ቢሮ (OTI) የተመረጠ፣ በሥራ ላይ የዋለ እና የሚደገፍ የኤሌክትሮኒክስ ውጤት መግለጫ መዝገብ ከመማሪያ ክፍል-ወደ-ቤት የመገናኛ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።

D. በክፍል ደረጃ እና ኮርስ የሚጠበቁ ነገሮች

የስርአተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ፅህፈት ቤት (Office of Curriculum and Instructional Programs (OCIP) የ MCPS ደንብ IFA-RA፣ ስርአተ ትምህርት፣ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት በክፍል ደረጃ የሚጠበቁ እና በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚጠበቁትን ኮርሶች የማዘጋጀት ሃላፊነት አለበት። ደረጃዎቹ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ደረጃዎች እና ምዘናዎች ወይም ሌሎች በአገር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁ መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

1. ሁሉም ተማሪዎች ለዲፕሎማ እንደሚሰሩ ይቆጠራሉ እናም በዚሁ መሰረት ተገምግመው ውጤት ይሰጣቸዋል፣ ይህም የሚሆነው የ IEP ቡድን ተማሪው(ዋ) ከስርአተ ትምህርቱ ጋር በተጣጣሙ የአማራጭ ትምህርት ላይ እንደሚማር/እንደምትማር፣ እንደሚገመገም እና እንደሚመዘን በማረጋገጥ ውጤቱ(ቷ) ወደ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት የሚያመራ ካልሆነ(ች) ነው። እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ ከወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ያስፈልገዋል፣ በሌላ መልኩ በሜሪላንድ የትምህርት አንቀጽ፣ ሰክሽን 8-405(ረ) ተካቷል "Annotated Code of Maryland, Education Article, Section 8-405(f)"።

2. በክፍል ደረጃ የሚጠበቅባቸውን ያላሟሉ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የተመደቡበትን ስርአተ ትምህርት የማስተካከል ሂደቶች በ OCIP፣ ከልዩ ትምህርት ቢሮ፣ የተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት፣ በማስተማር መማር እና ትምህርት ቤቶች ዋና ኃላፊ ጋር በመተባበር ይዘጋጃሉ።

E. የትምህርት ቤት ሥርዓቶች

1. የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት (OSSI) እና OCIP በትብብር የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲን IKA ተግባራዊ ለማድረግ በማስተማር፣ መማር እና ትምህርት ቤቶች ዋና ኃላፊ የተዘጋጁ የአፈጻፀም ሂደቶችን ይተገብራሉ። ከታች ሰክሽን III.J፣ K እና L ላይ እንደተገለጸው ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ፣ የውጤት ግምገማ እና/ወይም ማስተካከል/ማሻሻልን ይጨምራል።

2. የማርክ አሰጣጥ፣ የቤ ሥራ፣ ድጋሚ ማስተማር፣ እና የድጋሚ መመዘኛ ሂደቶች በት/ቤቶች ውስጥ በቋሚነት ይተገበራል። በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄዱ አሠራሮች በርእሰመምህር አማካይነት፣ ከትምህርት ቤት አመራር ቡድን ጋር በትብብር ይተገበራሉ።

3. ርእሰመምህራን ለሚከተሉት ሀላፊነት አለባቸዉ፡-

a) የማርክ አሰጣጥ፣ የሪፖርት አቀራረብና አፈፃፀም ሂደቶች በየት/ቤቶቻቸው በአግባቡ ተፈጻሚ መሆናቸዉን ማረጋገጥ። ርእሰመምህሩ(ሯ) በት/ቤት ውጤት ስለመስጠት እና የሪፖርት አቀራረብ ሂደቶችን ለማዘጋጀትና ለመቆጣጠር እንዲረዱት የትምህርት ቤቱን አመራር ቡድን ይሰይማል/ትሰይማለች፣ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

(1) ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ በመላው ትምህርት ቤት ወጥነት ያለው አሠራር ሊፈልጉ ይችላሉ፣ነገር ግን

(2) የክፍል- ደረጃ ወይም የኮርስ ቡድኖች ወይም ዲፓርትመንቶች ከዚህ በታች E.3 ላይ እንደተገለጸው ወጥ የሆነ የውጤት አሰጣጥ ሂደቶችን መመስረት አለባቸው።

b) በቅድመ-አገልግሎት ቀናት ውስጥ የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት የማድረግ ሂደቶችን ከሰራተኞች ጋር መገምገም።

c) በእያንዳንዱ ሴሚስተር መጀመሪያ ላይ ወይም የአሰራር ሂደቶች ሲቀየሩ የውጤት አሰጣጥ እና መረጃን ለወላጆች/አሳዳጊዎች በጽሁፍ ማሳወቅ።

d) ስለውጤት አመዘጋገብ እና የሪፖርት አሰጣጥ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚመለከተዉ የት/ቤት ሠራተኛ መመደብ እና የተመደበ(ች)ውን ሠራተኛ ስም ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች፣ ለወላጆች/ሞግዚቶች፣ እና ለ OCIP በየዓመቱ መጀመሪያ ላይ ማሳወቅ። የሚመለከተዉ የት/ቤት ሠራተኛ ስለ ማርክ/ውጤት አሰጣጥና ስለ ሪፖርት ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ የሚሰጥበትን ሁኔታዎች ማገናኘት እና እንደሚከተለው የማመቻቸት ሃላፊነት አለበ(ባ)ት፡-

(1) ጥያቄዎቹ የተወሰነን ተማሪ ዉጤት የሚመለከቱ ከሆነ አግባብ ወዳለው የትምህርት ቤት ባልደረባ መምራት

(2) ስለ ፖሊሲ እና የአሠራር ሂደቶችን በሚመለከት በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለርዕሰ መምህር ወይም ተወካይ ማሳወቅ

(3) ያልተመለሱ ወይም ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ወደ OCIP ማስተላለፍ

3. በየክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ ወይም የኮርስ ቡድን መምህራን ከሚከተሉት መካከል ወጥነት እንዲኖረው የመተባበር ሃላፊነት አለባቸው።

a) የተማሪዎቹ ውጤቶች የተመሰረቱባቸውን የማስረጃ ምንጭ፣ እና እያንዳንዱ አይነት ማስረጃ በምን ያህል ምጥጥን ለሴሚስተር ውጤት አሰጣጥ አስተዋፅዖ እንዳደረገ።

b) አስፈላጊ ከሆነ የምዘና ውጤቶችን አጠቃላይ ድምር፣

c) ከታች በሰክሽን III.F.3 እንደተገለጸው እንደገና የማስተማር እና የመገምገም ዕድሎች ዘዴ እና መርሃ ግብር።

d) በ MCPS ደንብ IKB-RA መሠረት በመካከለኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች ላይ በውጤት መስጫ ወቅት የቤት ሥራ በምን ያህል ድርሻ እንደሚቆጠር፣የቤት ሥራ ሂደቶች

4. ለመለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁለት የቤት ስራ ምድቦች የሚኖሩ ስለሆነ እንደሚከተለው በማርክ መስጫ ወቅት ይቆጠራሉ፡-

a) ለልምምድ ወይም ለመዘጋጀት የሚሠራ የቤት ስራ ከፍተኛው 10 በሙቶ የሚሆነውን ማርክ ሊይዝ ይችላል።

b) በመማር ላይ የተገመገመ የቤት ስራ በቀሪው የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ውጤት ላይ ይቆጠራል።

5. የሁለተኛ ደረጃ አስተማሪዎች ለሚከተሉት ሀላፊነት አለባቸው፡-

a) የማስረከቢያ ቀኖችንና የጊዜ/ቀነ ገደብ መወሰን።

(1) ለተማሪዎች የተሰጣቸዉን ሥራ ማጠናቀቂያ እድሎችን ለመጨመር ሲባል መምህራን የማስረከቢያ ቀን እና የማስረከቢያ ቀነ ገደብን/የመጨረሻ ሰአት እንዲለዩ/እንዲነጥሉ ይጠበቅባቸዋል።

(2) ከማስረከብያ ቀን በኋላና በጊዜ ገደብ (deadline) የቀረበ ስራ ከውጤቱ/ከማርኩ ከአንድ የፊደል ደረጃ ወይም ከ10 በሙቶ ባልበለጠ ዝቅ ሊደረግ ይችላል። ከጊዜ ገደብ በኋላ ገቢ የተደረገ ስራ ዜሮ ተብሎ ይመዘገባል።

b) ስለ እያንዳንዱ ኮርስ፣ ትምህርት፣ ወይም የውጤት ደረጃ የሚጠበቅባቸውን ለተማሪዎች እና ለወላጆች/ሞግዚቶች በጽሑፍ መግለጽ።

c) በሰክሽን III.1 እንደተገለጸው ውጤት የተሰጠባቸው ስራዎችን ለተማሪዎች መመለስ።

d) ተማሪው/ዋ የቀረ(ች)በት ምክንያት ምንም ቢሆን የማካካሻ (ማሟያ) ሥራ መፍቀድ። ተማሪዎች ከቀሩበት ሲመለሱ መምህራን ተመጣጣኝ፣ ግን የተለየ ስራ ወይም ተግባር ሊሰጧቸው ይችላሉ። ከህግ ውጭ ስለተከናወነ ከትምህርት መቅረት፣ ርእሰ መምህሩና የአመራሩ ቡድን ባፀደቁት አሠራር መሰረት፣ አስተማሪዎች ለጎደሉት ስራዎች ክሬዲት መንፈግ/መከልከል ይችላሉ።

e) የማስተማር፣ መማር እና የትምህርት ቤቶች ኃላፊ ባጸደቀው መሰረት፣ የውጤት አሰጣጥ ሚዛን በፊደል፣ በቁጥር፣ ወይም ምልክቶችን መጠቀም።

6. የሚከተሉት የማርክ/ውጤት አሰጣጦች የተከለከሉ ናቸው፡-

a) ተጨማሪ ክሬዲት እና/ወይም ጉርሻ/ቦነስ ነጥቦችን መስጠት።

b) ማርክ በድግግሞሽ ማጠጋጋት/Forcing grades ወይም ሌላ ማናቸውም ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር ማወዳደሪያ ስልት/curve መጠቀም።

c) ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር የሚያወዳድሩ የደረጃ አሰጣጥ መመዘኛዎችን መጠቀም (ያዘቀዘቁ ሚዛኖች አይፈቀዱም)።

d) ለአንድ ሥራ/ምዘና ከ 50 ፐርሰንት በታች ውጤት መስጠት። የሆነ ሆኖ ተማሪው/ዋ በተሰጠው (በተሰጣት) ሥራ/ምዘና ምንም ካልሰራ(ች) መምህራን ዜሮ መስጠት ይችላሉ። የተሰጠውን/የተሰጣትን ሥራ/መመዘኛ ተማሪው/ዋ መሠረታዊ መስፈርቶችን ለማሟላት ጥረት አለማድረጉ(ጓ)ን ወይም ተማሪው/ዋ በአካደሚ ማጭበርበር የተሳተፈ/ች መሆኑ(ኗ)ን መምህሩ/ሯ እርግጠኛ ከሆነ(ች) ዜሮ መስጠት ይችላል/ትችላለች።

e) ከ25 በመቶ በላይ ለሚሆነው የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የሚቆጠር ማንኛውንም ተግባር/ምዘና መስጠት።

F. ቅድመ-ምዘና፣ በትምህርት የታየ ለውጥ/Formative Assessment ግምገማ፣ ድምር/ማጠቃለያ ግምገማ/Summative Assessment፣ እና ዳግመኛ ግምገማ

1. ቅድመ-ምዘናዎች የተነደፉት ተማሪዎች ምን ያህል እንደሚያውቁ ለመገመት እና ማድረግ/መሥራት እንደሚችሉ አስቀድሞ ለማወቅና የሚማሩትን ትምህርት ለማቀድ ነው።

a) ቅድመ-ግምገማ ከትምህርት በፊት የሚካሄድ ሲሆን በመምህር እና በ MCPS የተዘጋጁ መመዘኛዎችን ያካትታሉ።

b) የቅድመ-መመዘኛዎች ውጤት ሊመዘገብ ይችላል ነገር ግን የተማሪው(ዋ)ን የማጠቃለያ ውጤት/ማርክ ለመወሰን በማስረጃነት አይያዝም።

2. በትምህርት ሂደት ውስጥ የተማሪን ትምህርቶችን የመቅሰም ችሎታ ለመመዘን ደረጃ የጠበቀ መመዘኛ ጋር የተጣጣሙ ፎርማቲቭ ምዘናዎች ይተገበራሉ። በትምህርት የታየ ለውጥ ግምገማ/Formative assessments መምህራንን በተከታታይ ስለሚያስተምሩት ትምህርት ለማሳወቅና ለመመራት የሚጠቅም ሲሆን በማስረጃነት ሊያዝ ይችላል።

3. የማጠቃለያ ምዘናዎች ተማሪዎች የተማሩትን መረዳታቸውን እና መተግበር መቻላቸውን ያረጋግጣሉ፣ ተማሪዎች በመለማመጃ ጊዜ ያገኙትን እውቀት/ችሎታ እንዲያሳዩ እድል ይሰጣል፣ በታወቁ መመዘኛዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን በዋናነት በግለሰብ ተማሪ አፈጻጸም ላይ ያተኩራል፣ አስፈላጊ ክህሎቶችን እና እውቀትን ለማዋሃድ ይረዳል።

a) የማጠቃለያ ምዘናዎች በመምህር ወይም በ MCPS የተዘጋጁ ፈተናዎች፣ በጽሑፍ የሚቀርቡ የጥናት ሥራዎች፣ ፕሮጀክቶች እና/ወይም የአፈጻጸም ትግበራዎችን ሊሆኑ ይችላሉ።

b) ከዚህ በታች ከተገለፀው ሁኔታ በስተቀር፣ የክፍል ደረጃ ወይም የኮርስ ቡድኖች መመዘኛ እና የድጋሚ ግምገማ ሂደቶችን ያዘጋጃሉ።

4. ዳግመኛ ግምገማ

a) በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት የአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ድጋሚ ካስተማሩ በኋላ እንደገና የመገምገም ዕድል ይሰጣቸዋል።

b) ሥራዎች/ግምገማዎች/ምዘናዎች እንደገና ሲገመገሙ፣ በመምህሩ(ሯ) ውሳኔ መሰረት በከፊል፣ ሙሉ በሙሉ፣ ወይም በተለየ ቅርጸት ሊገመገሙ ይችላሉ።

c) የዳግም ግምገማዉ ዉጤት የመጀመሪያውን ዉጤት ይተካል (በፊት ከተገኘዉ ውጤት የሚበልጥ ከሆነ)።

d) ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንደገና ሊገመገሙ የሚችሉ እና የማይችሉ ሁኔታዎች፡-

(1) በሚሰጡ ትምህርቶች ላይ የተማሪን የግስጋሴ ደረጃ የሚያመለክቱ ምዘናዎች ወይም ሥራዎች እንደገና ሊገመገሙ ይችላሉ።

(2) ትምህርት የመቅሰምን ችሎታ የሚያመለክቱ የሚከተሉት የትምህርት ሥራዎች እንደገና መገምገም አይችሉም፡-

(a) የኮርስ መጨረሻ ግምገማዎች፣ የማርክ መስጫ ወቅት ግምገማዎች፣ ወይም አስፈላጊ የሩብ አመት ግምገማዎች

(b) የመጨረሻ የምርምር ወረቀቶች፣ ሪፖርቶች፣ ወይም መጣጥፎች።

(c) የማጠቃለያ ፕሮጀክቶች ወይም አፈጻጸሞች።

G. ዲስትሪክት አቀፍ ግምገማዎች

በዲስትሪክት አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ተፈላጊ ምዘናዎች የመረጃው አንድ አካል ናቸው።

1. በተለየ የተመደበ ጊዜ፣ በተለየ የክፍል ደረጃ፣ እና የተለየ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን መመዘኛ ለመስጠት ዲስትሪክት አቀፍ ግምገማ ያስፈልጋል።

2. ዲስትሪክት አቀፍ ምዘና የሚሰጣቸው የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች፣ የተመረጡት ምዘናዎች ለውጤት መስጫ ክፍለ ጊዜ በ OCIP ድንጋጌ መሠረት በ10 ፐርሰንት ማርክ ሊሰላ ይችላል።

H. ለመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች/Seniors የማጠቃለያ ግምገማ

1. በእንግሊዝኛ/English፣ ኢሶል/ESOL፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ/ኮምፒውተር ሳይንስ/information technology/computer science፣ ሂሳብ/mathematics፣ ሳይንስ/science፣ የህብረተሰብ ጥናት/social studies፣ እና የዓለም ቋንቋዎች/world languages ኮርሶችን የሚወስዱ የመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች የመደምደሚያ አጠቃላይ ድምር ግምገማ (በአንዳንድ ሁኔታዎች ዲስትሪክት አቀፍ ፈተና ሊሆን ይችላል) ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል።

2. ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች የማጠቃለያ ግምገማ ውጤት የሚሰላው በአራተኛው የማርክ መስጫ ወቅት አማካይ ውጤት ሲሆን ለአራተኛው የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ 10 ፐርሰንት ይቆጠራል።

I. ውጤት የተሰጠበትን ሥራ መመለስ

1. ውጤት የተሰጠበት ሥራ ለተማሪዎች በተቻለ መጠን ቶሎ መመለስ አለበት።

2. ቴስቶች በኮምፒውተር የሚመዘገቡ ሲሆን ወይም የመልስ መስጫ ወረቀቶች ከቴስት ጥያቄዎች ተነጥለው ከሆነ፣ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በእጃቸው ካለ የቴስት ጥያቄዎች ጋር የማስተያየት እድል ሊኖራቸው ይገባል። ይህም ቢሆን ከዚህ በታች በተገለፀው መሰረት መምህራን ሁሉንም ጥያቄዎች እና ፈተናዎች ሁልጊዜ እንዲመልሱ የሚያስገድድ ሆኖ መተርጎም የለበትም።

3. ተማሪዎች ማርክ የተሰጠበትን ወረቀቶች ለሌላ ጊዜ ማመሳከሪያ ሊይዙት ይችላሉ እናም ወደየቤታቸው ወስደው (የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የግምገማ ውጤት ጭምር) ለወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው አሳይተው እንዲወያዩበት ይበረታታሉ። የተለዩ ሁኔታዎች/Exceptions ከታች ተገልጸዋል፦

   a) በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የአዘጋጁን ፍቃድና መብት ለመጠበቅ/copyright permissions፣ ወይም የቁሳቁሶቹን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ወይም ፈተናው በመገናኛ አውታር የሚሰጥ ከሆነና በሌላ መልክ ዳግም ማሠራጨት አስፈላጊ መስሎ ካልታየ መምህራን የፈተና ጽሑፎች/እቃዎችን ይዘው ለማቆየት ይችላሉ።

   b) መምህራን ማርክ የተሰጠባቸዉን ሥራዎች ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ለመገምገም (በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንደተለመደው)፣ በጊዜያዊነት ይዘው ሊያቆዩ ወይም ስነጥበብ እና እንግሊዝኛ የመሳሰሉ ክፍሎች ላይ እንደሚደረገው በናሙናነት ለመጠቀም፣ በጊዜያዊነት ይዘው ለማቆየት ይችላሉ።

4. ኮርሱ በተሰጠበት ወቅት ወይም ማርክ በሚሰጥበት ጊዜ ወላጆች/ሞግዚቶች የተማሪን የትምህርት ግስጋሴ ለማየት/ለማወቅ በግል ከጠየቁ፣ መምህራን ቴስቶችን እና አጫጭር ፈተናዎችን ወላጆች/ሞግዚቶች እንዲያዩ ያደርጋሉ። ውጤት/ማርክ የተሰጠውን ሥራ እንዲመለስ የሚደረግበት ምክንያት በምዘና ላይ ግልጽነትን ለማዳበር እና ለግለሰቡ(ቧ) ግብረመልስ ለመስጠት ነው። ሆኖም ይህ የምዘና ቁሳቁሶችን ደህንነት ከመጠበቅ ጋር ሚዛናዊ መሆን አለበት። ስለዚህ፣ ተማሪዎች እና ወላጆች/ሞግዚቶች የምዘና ማቴሪያሎችን ወይም ሌላ ውጤት/ማርክ የተሰጠባቸውን ሥራዎች ለሌሎች እንደማያጋሩ ወይም እንደማያሰራጩ ይጠበቃል።

J. ኮርስን ወይም የኮርሱን ክፊል እንደገና መዉሰድ

አንድ ተማሪ ከዚህ በታች ባሉት ሁኔታዎች መሠረት ክሬዲት የሚሰጥበትን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርስ ወይም ክፊል ኮርስ እንደገና መዉሰድ ይችላል/ትችላለች። ኮርሱን ወይም የኮርሱን ክፊል በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቅ/ስታጠናቅቅ፣ የተገኘዉ ውጤት ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው የተማሪው/ዋን የቀድሞ ዉጤት ሊተካ ይችላል።

1. ኮርስ እንደገና መዉሰድ

   a) የመጨረሻው ውጤት ምንም ይሁን ምን፣ አንድ ተማሪ ክሬዲት የሚሰጥበትን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ እንደገና መውሰድ ይችላል/ትችላለች።

b) ተማሪዉ/ዋ ያገኘ(ች)ው ከፍተኛው ውጤት በርእሰመምህር/ተወካይ አማካይነት በተማሪው(ዋ) ትራንስክሪፕት ላይ ተመዝግቦ የተመዘኑ እና ያልተመዘኑ አማካይ ውጤቶችን ነጥብ ለማስላት ተግባር ላይ ይውላል።

c) በ OCIP በተፈቀደው መሰረት ተማሪዎች የኮርስ ውጤትን በአንድ ኮርስ በተገኘው ውጤት መተካት የሚችሉት ተመሳሳይ ወይም ተመጣጣኝ የኮርስ ኮድ ሲኖረው ነው።

d) ክፍል ውስጥ ያለው ቦታ ውስን ከሆነ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ኮርሱን የሚወስዱ ተማሪዎች በድጋሚ ኮርስ ከሚወስዱ ተማሪዎች ይልቅ ቦታ የማግኘት ቅድሚያ ይኖራቸዋል።

e) የትምህርት ቤቱ ካውንስለር የተማሪው(ዋ)ን ውጤት ለማሻሻል MCPS Form 560-55 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርስ ማርክ የማስቀረት ማስታወቂያ።

2. የኮርሱን የተወሰነ ክፍል እንደገና መውሰድ (ክሬዲት ማሻሻል)

a) ለመመረቅ አስፈላጊ በሆነ የሴሚስተር ኮርስ የወደቁ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ በሚከተሉት የብቁነት መስፈርቶች መሰረት፣ ዉጤታቸዉን ወደ ማለፊያ ደረጃ D ለማሳደግ እና የኮርስ ክሬዲት ለማሻሻል፤ ከኮርሱ የወደቁበትን ክፍል እንደገና ሊወስዱ ይችላሉ፡-

(1) በሰክሽን III.B.7.d ያለው የውጤት ሰንጠረዥ ለክሬዲት ማሻሻያ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉትን ሁለቱን የውጤት ሁኔታዎች ያሳያል።

(2) የአንድ ኮርስ ማርክ የሚሰጥበትን ሴሚስተር ሁለተኛ የማርክ መስጫ ወቅት ለወደቁ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ክሬዲት ማሻሻያ እድል ይኖራል። በልዩ ሁኔታዎች ምክንያት፣ በርእሰ መምህሩ(ሯ) እና የሚመለከተው OSSI ተወካይ ፈቃድ፤ አንድ ተማሪ በሴሚስተር የመጀመሪያ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ E ላገኘ(ች) ተማሪ በሁለተኛ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ E ካገኘ(ች) እንደገና ክሬዲት እንዲያሻሽል/እንድታሻሽል ሊፈቅዱለት ይችላሉ።

(3) ሁሉንም የማርክ መስጫ ጊዜ አላማ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቁ(ቋ)ን ለማሳየት የክሬዲት ማሻሻያ ኮርስ በመመዝገብ/በመውሰድ ብቻ ማግኘት ይቻላል።

(4) "Regulation JEA-RA" ላይ በተቀመጠው መሰረት፣የተማሪ ትምህርት ላይ መገኘት የክትትል ጣልቃ ገብነት እቅድ ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ፣ ትምህርት ላይ ባለመገኘት ምክንያት ስኬታማነትን ባለማሳየት የመዉደቂያ ዉጤት ላገኘ/ች ተማሪ፣ የክሬዲት ማሻሻል እድል አይኖርም/አይፈቀድም።

b) ከማዕከል የሚሰጥ የኦንላይን ክሬዲት ማሻሻያ ሞጁል ለማይኖራቸው ኮርሶች፣ የት/ቤቶች የበላይ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ በአካባቢው ትምህርት ቤት የሚሰጡትን የክሬዲት ማሻሻያ ማቴሪያሎችን መፍቀድ ይችላል/ትችላለች፣ የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ስራ ውጤት የሚያሳዩ ተገቢ ሰነዶች ሁሉንም የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ዓላማዎች በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ በ OCIP የሚቀርብ እና የሚገመገም መሆን አለበት።

c) ተማሪው/ዋ የማርክ መስጫ ወቅት ዓላማዎችን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቁ/ቋን ካሳየ/ች፣ በድጋሚ የተወሰደዉን ሥራ ዉጤት ለማንፀባረቅ የተማሪው/ዋ የማርክ መስጫ ወቅት ዉጤት እንዲሻሻል ይደረጋል።

d) የትምህርት ቤት ካውንስለሮች ተማሪዎችን ይረዳሉ–

(1) የክሬዲት ማሟያ መስፈርቶቻቸውን ለማሟላት ተገቢ ኮርሶችን መውሰድ አለባቸው፣ ይህም የሠመር ትምህርት ወይም በማዕከል የሚዘጋጁ ኦንላይን ኮርሶችን ሊያካትት ይችላል፣ እና

(2) በመጀመሪያው ሴሚስተር የመጀመሪያ ማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ E እና በሴሚስተር ሁለተኛ ማርክ መስጫ ጊዜ E ካገኙ በኋላ የማገገሚያ ክሬዲት መውሰድ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ከርእሰመምህር እና ከ OSSI ፈቃድ የማግኘት ሂደቱን ያስጀምሩ።

(3) የትምህርት ቤቱ ካውንስለር የተማሪው(ዋ)ን ውጤት ለማሻሻል MCPS Form 560-55፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርስ ማርክ ማስወገድ ማስታወቂያ ቅጽ ይሞላል።

(4) ርእሰ መምህሩ/ተወካይ የኮርስ ውጤቱን በተማሪ የመረጃ ቋት ላይ እንዲሻሻል ለማድረግ - የክፍል ውጤት ሪፖርት ማድረጊያ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማርክ እርማት ሞጁል ቅጹ በርዕሰ መምህሩ መጽደቅ አለበት። አንድን ውጤት ከ E ወደ D ለማሻሻል እና የቀደመውን ውጤት ለማስወገድ ዶክመንቱን መከለስ እና ተማሪው(ዋ) የክሬዲት ማሟያ ኮርስ የወሰደ(ች)በት ሴሚስተር ካለቀ በ 45 የትምህርት ቀናት ውስጥ ርእሰመምህሩ ውሳኔ መስጠት አለበት።

(5) ተማሪው/ዋ ለክሬዲት ማሻሻል የተመዘገበ(ች)በት መምህር የተለየ ከሆነ፣ የተማሪው/ዋ ውጤት በተገኘዉ ክሬዲት ማሻሻያ ሲተካ ለቀድሞው መምህር መገለጽ አለበት።

(6) የ MCPS Form 560-55 ቅጂ ለመምህሩ እና ለት/ቤት ካውንስል ጽ/ቤት በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት እንዲቀመጥ ይሰጣል።

K. ዉጤት ማስተካከያ

ተማሪው(ዋ) በክፍል ደረጃ ወይም በኮርስ የሚጠበቀውን ውጤት በመጨረሻ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ወይም ሴሚስተር ከተመለከተው የተማሪ አፈጻጸም ደረጃ ውጤት የኋላእኛው እንደሚሻል የሚያሳይ ማስረጃ ሲኖር፣ ውጤቱ ሊሻሻል ይችላል።

1. ዉጤትን ለማሻሻል ምክንያቶች፣በዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የዉጤት አሰጣጥ እና የሪፖርት አቀራረብ ሂደቶችን/አሠራሮችንና የአፈፃፀም ስህተቶችን ማረምን ያካትታል።

2. ወዲያውኑ የውጤት ማሻሻያ እድል ሊሰጥ የሚችለው ላለፈው የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ወይም ሴሚስተር ብቻ ነው። የውጤት ማሻሻያ ለመጠየቅ የቀረበውን ሰነድ መከለስ እና እንደአስፈላጊነቱ የማርክ መስጫ ጊዜው ወይም ሴሚስተር ካለቀ በ45 የትምህርት ቀናት ውስጥ ርእሰመምህሩ ውሳኔ መስጠት አለበት። የአራተኛ ማርክ መስጫ ጊዜን ወይም የስፕሪንግ

ሴሚስተር ኮርሶችን ለማሻሻል የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መከለስ እና በሚቀጥለው የትምህርት አመት መጀመሪያ በ 45 የትምህርት ቀናት ውስጥ ርእሰመምህሩ ውሳኔ መስጠት አለበት።

3. ከዚህ በታች በሰክሽን III.K.6 እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር፣ የተማሪ ዉጤት ማሻሻል አስፈላጊ ከሆነ መከናወን ያለበት በአስተማሪው(ዋ) ነዉ፣ ሆኖም በተማሪ የመረጃ ቋት ውስጥ የተማሪ ውጤት ሪፖርት ማቅረቢያ ሞዱል ከመቀየሩ በፊት በርእሰመምህር መጽደቅ አለበት። የተማሪ ዉጤት ሲሻሻል ለአስተማሪው(ዋ) ማሳወቅ ያስፈልጋል።

4. ለመካከለኛ ወይም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የማርክ መስጫ ወቅት ወይም የሰሚስተር ዉጤትን ስለማሻሻል–

   a) ጠያቂው(ዋ) (ማለትም፦ መምህር ወይም ርእሰመምህሩ ከመምህር ጋር በመመካከር) MCPS Form 355-27A፣የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውጤት ማሻሻያ፣እና የውጤት ማሻሻያ ጥያቄውን ለርዕሰ መምህር ማቅረብ አለባቸው።

   b) ርእሰ መምህሩ/ተወካይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት በተማሪው የመረጃ ቋት ሪፖርት ማቅረቢያ ሞጁል ውስጥ የኮርስ ውጤቱ(ቷ) እንዲሻሽል MCPS Form 355-27A በርዕሰ መምህር መጽደቅ አለበት፣ እና

   c) በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት MCPS Form 355-27A ቅጂው ለመምህሩ(ሯ) እና ለት/ቤቱ ካውንስል ቢሮ ይሰጣል።

5. በተቀመጡት የአሠራር ቅደምተከተሎች መሰረት፣ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የማርክ መስጫ ወቅት ዉጤት ለመቀየር መምህር እንደ አስፈላጊነቱ ሰነዶችን ያቀርባል/ታቀርባለች፣ እናም ርእሰምምህር/ተወካይ በተማሪው/ዋ የመረጃ ቋት ውስጥ በዉጤት ሪፖርት ማድረጊያ ሞጁል ላይ የተሻሻለው የኮርስ ውጤት እንዲቀየር ያደርጋል/ታደርጋለች።

6. የዉጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት የማድረግ ሂደቶችን ለመተግበር መምህራን ሀላፊነት አለባቸው። በቦርድ ፖሊሲ IKA፣ ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ፣ በዚህ ደንብ እና ይፋ በተደረገ መመሪያ መሰረት ሂደቶች ካልተገበሩ በጉዳዩ ላይ አንድ ርእሰመምህር ከመምህሩ(ሯ) ጋር በመመካከር ተገቢውን ሰነድ በማዘጋጀት የውጤት ደረጃ ማሻሻል ይችላል/ትችላለች።

L. ይግባኝ

1. ከቦርድ ፖሊሲ KLA ጋር በሚስማማ ሁኔታ በዉጤት ላይ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል ፣ለሕዝብ ጥያቄዎች እና አቤቱታዎች ምላሽ ስለመስጠት።

2. MCPS Regulation KLA-RA ቅሬታዎችን ለመፍታት የተቀመጡ መደበኛ እርምጃዎች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ ስለመስጠት፣ በአከባቢው ትምህርት ቤት ቅሬታዎችን ለመፍታት መደበኛ ያልሆኑ አካሄዶች ካልተሳኩ መወሰድ ያለባቸው መደበኛ እርምጃዎች። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እነዚህ መደበኛ ያልሆኑ አቀራረቦች ከሪሶርስ መምህሩ/ሯ /የይዘት ባለሙያ ጋር ምክክርን ሊያካትት ይችላል።

M. ግምገማና ዘገባ

1. በየዓመቱ OSSI፣ OCIP እና OTI በዚህ ደንብ ውስጥ የተቀመጡትን ሂደቶች እና የጊዜ ገደቦች መከበራቸውን ለመገምገም የውጤት ማሻሻያዎችን፣ ኮርሶችን እንደገና የመውሰድ ሒደት እና

ክሬዲት ስለማሻሻል ይቆጣጠራሉ። MCPS Regulation JEA-RA፣ ተማሪ በትምህርት ላይ ስለመገኘት፣ እና የሜሪላንድ የተብራራ ደንብ ኮድ Maryland Regulations (COMAR) §13A.03.02.08B(5)።

2. እንዲህ ዓይነቱ ቁጥጥር በት/ቤቶች በሙሉ እና በት/ቤት ደረጃዎች (ማለትም፣ አንደኛ ፣ መካከለኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች) ተገቢውን የተማሪ ሬኮርዶች ናሙና ሪኮርድ ግምገማን ያካትታል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Individuals with Disabilities Education Improvement Act of 2004፤34 CFR Section 300.320፤ Annotated Code of Maryland፤Education Article §8-405(f)፤Code of Maryland Regulations§13A.03.02.08 እና §13A.05.01.09(B)

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡-** የበፊት ደንብ ቁ. 3554፣ ኦክቶበር 30, 1981 ዓ.ም. ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል፣ ጁን 10,1988 ተሻሽሏል። ኖቨምበር 2, 1993 ተሻሽሏል። ኦክቶበር 1, 1996 ተሻሽሏል። ኦገስት 5, 2008 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ ሜይ 12፣ 2010 ተሻሽሏል፣ ጁን 27, 2016 ተሻሽሏል፣ ጁን 28, 2017 ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 24, 2019 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 27, 2022 ተሻሽሏል።